# ለእቅዱ ስኬት ጋምቤላና የሰፋፊ እርሻ ልማት ሥራ

ፋኖሴ ከአራት ኪሎ /ክፍል ሁለት/

ከፍተኛ የካፒታል እጥረት ባለባት አገራችን የውጭ ባለሃብቱ የተትረፈረፈ የካፒታል ክምችት እጥረቱን በመቅረፍ የኢንዱስትሪ ልማታችንን ሊያፋጥን እንደሚችል ግልጽ ነው፡፡ የዓለም ገበያን ሰብሮ የመግባት ልምድና ችሎታው በሌላት አገራችን የውጭው ባለሃብት ጠንካራ አላማዊ የገበያ መረብ የውጭ ገበያውን ሠብሮ ለመግባት የቀለለ መረማመጃ ሆኖ ሊያገለግለን እንደሚችልም ግልጽ ነው፡፡ ከፍተኛ የቴክኖሎጂና የአመራር ብቃት ጉድለት በሚታይባት አገራችን የውጭው ባለሀብት የዘመናዊ አመራር የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ችሎታን እንደሚያስተላልፍልንም ይታመናል፡፡ የውጭ ባለሃብቱ ሊያስገኝልን የሚችለውን እነዚህን ጥቅሞች አሟጦ ከመጠቀም ውጪ ፈጣን የኢንዱስትሪ ልማት የማረጋገጥ አላማችን በፍፁም ሊሣካ እንደማይችል አብዛኞቻችን ያሰመርንበት እውነታ ነው፡፡

ከውጭ ባለሀብቱና ኢንቨስትመንቱ ጋር ተያይዞ በተለይም በሠፋፊ የእርሻ ልማት ሥራ ላይ የሚሠማሩትን በተመለከተ በርካታ አስተያየቶች ሲሠጡ መቆየታቸው ይታወሳል፡፡ አሁንም አስተያየቶቹ እንደቀጠሉ ነው፡፡ የአስተያየቶቹ ዋነኛ ማጠንጠኛ ደግሞ የመሬት ወረራና የደን ምንጣሮን / የአካባቢ ጥበቃን/ የተመለከቱ ናቸው፡፡ በዚህ ስር በተለይም አዳጊ በሚባሉት ክልሎች ለውጭ ባለሃብቱ የሚሠጠው መሬት ባልተጠና መንገድና አካባቢን የሚያራቁት ነዋሪዎችንም ለሥደት የሚዳርግ እንደሆነና የባለሃብቶቹ ፍላጐት ኢንቨስትመንት ሳይሆን የመሬት ሽሚያ ነው የሚሉት አስተያየቶች የሚበዙ ናቸው፡፡ ይህን በተመለከተ የመንግሥትን ተሣትፎ የሚተቹ መንግስት ለዜጐቹም ሆነ ለሃገሪቱ ደንታ ቢስ እንደሆነ የሚያስቆጥሩ አስተያየቶችና ጉዳዩ የበለጠ ለድህነት የሚዳርግ እንደሆነ የሚያሳስቡ ሙያዊም ሙያዊ ያልሆኑም፣ ፖለቲካዊና መሠል ተልእኮዎች ያላቸው አስተያየቶችን ስናነብና ስናደምጥ ከርመናል፡፡ ይህንኑ ጉዳይ መነሻ በማድረግ ሠፋፊ የእርሻ ልማት ይከናወንባቸዋል ከሚባሉት ክልሎች አንዱ የሆነው የጋምቤላ ክልል ያደረኩትን የኢጋጣሚ ጉዞ በመጠቀም ሙያዊ እይታና መረጃ በመሰብሰብ የክልሉን የኢንቨስትመንት ጉዞና

የውጭ ባለሃብቱን ተሳትፎ በተመለከተ “ለእቅዱ ስኬት የጋምቤላ ክልል ሠፋፊ የእርሻ ልማት ሥራዎች” በሚል ርእስ አስነብቤያችሁ እንደነበር እንደምታስታወሱ አገምታለሁ፡፡ በዚህ ጽሁፌ ማጠቃለያም ላይ በተለይም ስፋት ያለው አስተያየት የሚሰጥበትን የመሬት አያያዝ በተመለከተ በተጨማሪ ደግሞ የክልሉን የመንደር ማሰባሰብ ፕሮግራም በተመለከተ በቀጣይ ክፍል ላስነብባችሁ ቃል ገብቼ ነበር፤ እነሆ ቃሌን ጠብቄ በዛሬው ጽሑፌ እውነት እንደሚባለው የጋምቤላ መሬት የውጭ ባለሃብቱ ሰለባና ለዘፈቀደ ወረራ የተጋለጠ ነው? ወይስ በመግቢያዬ እንደጠቀስኩት ለቀጣዩ የኢንዱስትሪ ልማት ጉዞአችን በሚጠቀም መንገድ መሬቱን እየተጠቀምንበት ነውን? የሚሉትን ጥያቄዎችና የመንደር ማሰባሰብ አስፈላጊነቱንና የሥራ ሂደቱን በተመለከተ ለመላው ህብረተሰብና በቀጣይም በክልሉ ኢንቨስት በማድረግ የህዳሰው አካል ለመሆን ለሚሻ ባለሃብት በሚቀጠቅም መልኩ ተከታዩንና ተጨባጩን መረጃ እነሆ እላለሁ፡፡

በእቅድ የተመራና ፍትሃዊ የሆነ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀምን ተግባራዊ በማድረግና የአካባቢ ብዝሃ ህይወት ሃብት ጥበቃ ሥርዓትን በመዘርጋት መሬትን በአግባቡ በመጠቀም ለኑሮና ለልማት ምቹ የሆነ አካባቢን በመፍጠር ዘላቂ ልማትን ማረጋገጥ እንደሚቻል ብዙዎቹ የዘርፉ ባለሙያዎች የሚስማሙበት እውነታ ነው፡፡ ለኢንቨስትመንት በሚሰጥ መሬት፣ በተፋሰስ ልማት፣ በብዝሃ ህይወት ሃብት ልማትና ጥበቃ፣ በተፈጥሮ ሃብት ልማትና ጥበቃ እንዲሁም የደረቅና ፈሣሽ ቆሻሻ አወጋገድ የሥራ ሂደቶችን ማቀናጀትና በሥርዓት መምራት ለምናስበው የዘላቂ ልማት ሥራ የሚኖረው አስተዋጽኦ ከፍተኛ እንደሆነም እነዚሁ የዘርፉ ባለሙያዎች የሚስማሙበት ሁለተኛው ሃቅ ነው፡፡

ስለሆነም በሀገር ደረጃ የመሬት አስተዳደር አጠቃቀምና የአካባቢ ጥበቃ መረጃን የሚያዘጋጅ የሚያደራጅና የሚያስተዳድር አካል እና ማንኛውም ልማት የመሬት አጠቃቀም እቅድና የአካባቢ ጥበቃን ባገናዘበና በተቀናጀ አኳኋን ለማካሄድ በባለቤትነት የሚመራ አካል ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ በፌደራል የግብርና ሚኒስቴር ሥር አንድ የባለሥልጣን ቢሮ ተቋቁሞ ሥራውን ከጀመረ ሰነባብቷል፡፡ ቢሮው ከክልሎች ጋር በሚኖረው የተቀናጀና በመናበብ ላይ የተመሠረተ ሥራው በርካታ ኪራይ ሰብሳቢዎችን ከልማታዊ ባለሀብቱ መነጠል ችሏል፡፡ ይህንኑ አሠራርና

ተሞክሮ በመጠቀም ሠፋፊ የሆኑ የእርሻ መሬቶችን በተገቢው መንገድ ለመጠቀምና የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱን ለማሣካት እንዲቻል የጋምቤላ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በኢንቨስትመንት ቢሮ ውስጥ ተከማችተው የነበሩትንና ከበርካታ የኢንቨስትመንት ዘርፎች ጋር ተደባልቆ የነበረውን መሬት በመነጠል በተገቢው መንገድ ሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችለውን አቅጣጫ አስቀምጧል፡፡ በዚሁ መሠረት በጋምቤላ ክልል የገጠር መሬትን በተቀናጀ መልኩ ለማስተዳደርና "የመሬት አጠቃቀም እቅድ የማዘጋጀት ሥልጣን ያለው አካል የመሬት አጠቃቀም አስተዳደር እና አካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን በአዋጅ ተቋቁሞ ሥራውን ጀምሯል፡፡

የመሬት ይዞታና የመጠቀም መብት ዋስትና የመስጠት በመሬት ዙሪያ ለሚነሱ አቤቱታዎች ተገቢና ቀልጣፋ መፍትሔ መስጠት፣ ይዞታን በውርስ በስጦታ፣ በኪራይና በልውውጥ ማስተላለፍ አዳዲስ የይዞታና የመጠቀም መብትን መለየትና መስጠት፣ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ሥርዓት ግንባታ ላይ ግንዛቤ መፍጠር፣ የአካባቢ ተጽእኖና ስልታዊ የአካባቢ ግምገማ ማድረግ፣ የአካባቢ ኦዲትና የብክለት ምርመራና የአካባቢ ትምህርትና ሥልጠና መስጠት እንዲሁም በብዝሃ ህይወት ሃብት ጥበቃ ልማትና አጠቀቀም ላይ የህብረተሰቡን ግንዛቤ ማዳበር የፕሮጀክት ዝግጅትና የሙያ ድጋፍ ክትትል ግምገማ፣ ቁጥጥርና መሠል ጉዳዮች የባለስልጣኑ ኃላፊነትና አገልግሎቶች ናቸው፡፡

ካፒታልንና ተፈላጊ ቴክኖሎጅን እንዲሁም የሃገሪቱን የልማት እቅድ ከማሳካት አኳያ የውጭ ምንዛሪ በሚያስገኙ የልማት ዘርፎችና ለኢንዱስትሪው እድገት አስተዋጽኦ ያላቸውን ሰብሎች የሚያመርቱ ባለሃብቶችን በተመለከተ ባለሥልጣኑ ከግብርና ሚኒስቴር የመሬት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ጋር በጋራና በቅንጅት ይሠራል፡፡ በዚህ ቅንጅታዊ አሰራርም በክፍል አንድ ያስነበብኳችሁ ውጤቶች ተገኝተዋል፡፡ ለማስታወስ ያህል 434 በግብርና የተሠማሩ ባለሃብቶች ሥራ ውስጥ ገብተዋል፡፡ 2,446,821,294 (ሁለት ቢሊዮን አራት መቶ አርባ ስድስት ሚሊዮን ስምንት መቶ ሃያ አንድ ሺህ ሁለት መቶ ዘጠና አራት ብር) ያስመዘገቡት ካፒታል ነው፡፡ ፕሮጀክቶቹ ለ22,428 ቋሚና ለ 143,752 ጊዚያዊ ሠራተኞች የሥራ እድል መፍጠራቸው ደግሞ ለትራንስፎርሜሽን እቅዱ ስኬት ያላቸውን ፋይዳ ያጐላዋል፡፡ በመግቢያዬ ለመጠቆም

እንደሞከርኩት የውጭ ባለሃብቶች ካላቸው ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ አንፃር 162,500 ሄክታር የገጠር መሬት ለአምስት የውጭ ባለሃብቶች ተላልፏል፡፡

ለሩዝ፣ ሸንኮራ አገዳና ፓልም ምርት የሚሆን 100,000 ሄ/ር ካራቱሪ ለተባለ ኩባንያ፣ ለፓልምና የቅባት እህል 27,500 ሄ/ር ለቢ.ኤች.ኦ፣ ለጥራጥሬና አኩሪ አተር /ገና በምንጣሮላይ ያለ /25,000 ሄ/ር ለሩቺ ካምፓኒ፣ 10,000 ሄ/ር የሩዝ ምርት ተግባር ላይ የዋለና 350 ሄ/ር ለዘር የተዘጋጀ መሬት ለሳውዲ ስታር ኩባንያ ተላልፏል፡፡ እነዚህ የውጭ ባለሃብቶች ልክ እንደተባለው በመሬት ሽሚያ ላይ? ወይስ በተግባር የሥራ እንቅስቃሴ ውስጥ ናቸው? በአካባቢው ላይ ያሳደሩት ተፅዕኖ አሉታዊ ወይስ አዎንታዊ? ጋምቤላ ከነዚህ ባለሃብቶች ምን ተጠቀመ? ስል የባለስልጣኑን ኃላፊ አቶ ሃይለማርያም ጠይቄ ተከታዩን ምላሽ ሰጥተውኛል፡፡

በሃገራችን በስፋት ያልተለመዱ የሰብል አይነቶች ዘራቸውንና ቴክኖሎጂውን በማስገባት የአካባቢው ህብረተሰብ እንዲለምደውና ወደፊትም ማልማት እንዲቻለው ሙከራ እየተደረገ ሲሆን ባለሀብቶቹ የአካባቢውን ማህበረሰብ አደራጅተው ወደልማት የማስገባትና ድጋፍ የማድረግ ሥራ በመስራት ላይ ናቸው፡፡ የክልሉ መግንግስት እያደረገ ያለውን የመንደር ማሰባሰብ ሥራ በማገዝ በኩልም ሁለንተናዊ ድጋፍ አድርገዋል፡፡ አምስት ሚሊዮን ብር በመመደብ ስታዲየም በመገንባት ላይ ሲሆኑ ለወጣቱ የተሻለ የሥራ አድልም ፈጥረዋል፡፡ የተፈጥሮ ሃብት ሚዛንን ከመጠበቅ አንፃር ችግኞችን በመትከልና የችግኝ ጣቢያ በማቋቋም ቃላቸውን ጠብቀዋል፡፡ ልማታዊነታቸውንም አረጋግጠዋል፡፡ ለዚህ ነው እርስ በርሱ የተያያዘና የተደጋገፈ ሥራ ለእቅዱ ስኬት ያለው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው ስል በተደጋጋሚ ለመግለጽ የሞከርኩት፡፡ በጋምቤላ ክልል በሚገኙ ሠፋፊ የእርሻ ልማት ሥራዎች ላይ በተለይም ከተማረ የሰው ኃይል አንፃር /በተለይም የተፈጥሮ ሃብት ጥበቃ/ እና በሌሎችም የግብርና ዘርፎች ጥቃቅን ችግሮች ቢኖሩም "የሚያጠግብ እንጀራ ከምጣዱ ያስታውቃል" እንዲሉ አያያዙ ትልቅ ተስፋ እንድሰንቅ አስችሎኛል፡፡ በጋምቤላ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ድህነትን በመዋጋት ሥትራቴጂ ውስጥ ዋነኛው አጀንዳ የመንደር ማሰባሰብ ሥራ ነው፡፡ ለመሆኑ ነዋሪውን በመንደር ማሰባሰብ ያስፈለገው

አንዳንድ ግለሰቦች እንደሚሉት ከቄያቸው ለማፈናቀል ነው? ወይስ ሌላ የማናውቀው ምክንያት ይኖር ይሆን?

የመንደር ማሰባሰቡ ሥራ አስፈላጊ ሆኖ የተገኘው ህብረተሰቡ በሁሉም የልማት ዘርፎች የሚፈለገውን ግልጋሎትና ጠቀሜታ ማግኘት ባለመቻሉና ማህበረሰቡ በተንጣለለ ሃብት ላይ ተቀምጦ የምግብ ዋስትናውን ባለማረጋገጡ ምክንያት ሲሆን ለዚህም አስተዋጽኦ ያደረገው በአንድ አካባቢ በሚኖረው እርሻና እርባታ ላይ የተመሠረተ የአሠራር ዘይቤ፣ የተፈጥሮ ደንን እየመነጠሩ ለተዘዋዋሪ እርሻ መጠቀም ፣ የወንዝ እርሻ ዳርን በመከተል እርሻ ማካሄድ፣ አሣ በማስገር ላይ ብቻ ኑሮን መመስረት፣ በማር ማነብ ተግባር ላይ ብቻ ማትኮር፣ እና የመሳሰሉት ምክንያቶች ህዝቡን ለከፋ ድህነት እና ጉስቁልና ዳርገውታል፡፡ የወንዝ ዳርቻ እርሻ ኑሮአቸውን ወራጅ ወንዝ ተከትሎ እንዲመሠረት ያደረገ በመሆኑ በየጊዜው ህብረተሰቡም ሆነ የሚያረቡት እንስሳትና የሚዘሩት ሰብል ለአደጋ ተጋልጠው ቆይተዋል፡፡ ለተዘዋዋሪ እርሻ ጥቅም ሲባል የተፈጥሮ ደንን መመንጠር አካባቢውን ለአፈር ብክለትና የአየር መዛባት የዳረገ በመሆኑ በምርትና ምርታማነት ላይ የበኩሉን ተጽእኖ አሣድሯል፡፡ በተጨማሪም ማህበረሰቡ ተበታትኖ በመኖር ዘይቤው ለሰው ሰራሽ አደጋ እንዲጋለጥ ሆኗል፡፡

መንግስት መንግስታዊ ያለሆኑና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች እንዲሁም ልማታዊ ባለሃብቶች ከሚዘረጓቸው የመሠረተ ልማት ውጤቶች / መስኖ፣ መንገድ፣ መብራት፣ ፖስታ፣ ቴሌና ገበያ/ እና ማህበራዊ አገልግሎት መስጫ ተቋማት /ትምህርት የእንስሳትና የሰው ጤና ኬላዎች፣ የገንዘብ ተቋማት፣ ወፍጮና መጋዘን፣ የመጠጥ ውሃ አገልግሎት ወዘተ../ ነዋሪው ተጠቃሚ መሆን ያለመቻሉና መንግስታዊ አደረጃጀቶችን በመዘርጋት ተገቢውን ድጋፍና ክትትል ለማድረግ እንደዚህም መልካም አስተዳደርን ለማስፈን ተደራሽ ሆኖ ያለመገኘቱ በሌሎችም ተያያዥ ምክንያቶች የክልሉ ነዋሪዎችን በመንደር የማሰባሰቡ ስራ ተግባራዊ ሆኗል፡፡ የክልሉ መንግሥት የመንደር ማሰባሰብ ሥራውን የጀመረው ዝም ብሎና በዘፈቀደ ሳይሆን ለተግባራዊነቱ አስተማማኝ የሆኑ መረጋገጥ መነሻዎችን ይዞ ነው፡፡

የመንደር ማሰባሰብ ፕሮግራም ከመጀመሩ በፊት በመንደር መሰብሰብ ሊያስገኝ በሚችለው ኢኮኖሚያዊ ፖለቲካዊ ማህበራዊና አካባቢያዊ እንደዚሁም በዘላቂ ልማትና ምግብ ዋስትና መረጋገጥ ስላለው ፋይዳና ጠቀሜታ በየደረጃው ያሉ የአመራር አካላት ግንዛቤ እንዲያገኙ በመደረጉ ፕሮግራሙን በቁርጠኝነት ለማስፈጸም ተነሣሽነት ያላቸው መሆኑ የመጀመሪያው ሲሆን፤ በመንደር ከሚሰበሰቡት የማህበረሰብ አካላትና የአካባቢ ሽማግሌዎች እንደዚሁም ጐሳ መሪዎች ጋር ፕሮግራሙን በጋራ ለመፈፀም የሚያስችል የምክክር መድረክ በመፍጠር ስምምነት ላይ የተደረሰ መሆኑና በመንደር ለመሰባሰብ ከማህበረሰቡ ጥያቄዎች መቅረባቸው ደግሞ ሌሎች መነሻዎች ናቸው፡፡

በዚሁ መሠረት በአመራሩ ቁርጠኝነትና በህዝቡ ጥያቄ መነሻ በጋራ መግባባት ላይ የተደረሰበት የመንደር ማሰባሰብ ወይም በአንድ አመት 15ሺህ ነዋሪዎችን በመንደር ለማሰባሰብ በክልሉ መንግስት በእቅድ ቢያዝም በተየዘው አመት አጋማሽ ላይ ብቻ በፈቃደኝነት የተመዘገበው ህዝብ 26,662 ደርሷል፡፡ ለነዚሁ ሰፋሪዎች 15,400 ቤት ተገንብቶ ለነዋሪዎቹ ተላላፏል፡፡

የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር አቶ ዑመድ ኡባንግ ለጋዜጠኞች እንደተናገሩት የመንደር ማሰባሰብ ፕሮግራም ሲታቀድ ህዝቡን የመሠረተ ልማት ተጠቃሚ፣ የዘመናዊ እርሻ ተጠቃሚ ለማድረግና በየጊዜው የሚገጥሙን የጐርፍ ችግር ለማስወገድ ነው፡፡ በተቃራኒው የልማት ትግሉን ለማደናቀፍ የሚጥሩ ፀረ ልማት አጀንዳ የሚያራምዱ ሃይሎች መሬቱን ለግል ኢንቨስተር ለመስጠት ነው እያሉ የሚያናፍሱት ወሬ ከወሬነት እንዳያልፍ አድርገናል፡፡ ስለሆነም ይህ የመንደር ማሰባሰብ ፕሮግራም አሁን በተጀመረው መንገድ ከተጠናቀቀ የምግብ ዋስትናው በክልሉ በአካባቢና በቤተሰብ ደረጃ ይረጋገጣል የሚል እምነት አለኝ ብለዋል፡፡

በ50 የመንደር ማእከላት የማሰባሰቡ ሥራ እየተከናወነ ሲሆን ከአኮቦ ወረዳ በስተቀር የሁሉም ወረዳ ነዋሪዎች በመንደር የሚሰባሰቡ ናቸው፡፡ ሂደቱን በተመለከተ ሥራው በአግባቡ እየተከናወነ መሆኑን ለመለየትና ለሚገጥሙ ችግሮች ድጋፍ ለማድረስ በክልሉና በፌዴራል ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች ማእከላቱ በተከታታይ ይጐበኛሉ፡፡

ለነዚሁ በመንደር ለሚሰባሰቡ ነዋሪዎች በምግብ እራሳቸውን እስኪችሉ ድረስ ለስምንት ወር የምግብ አቅርቦት የሚደረግ ሲሆን ከሶስት እስከ አራት ሄ/ር መሬት በቤተሰብ ደረጃ ለአርሶ አደሩ ይሰጣል፡፡ በባለሙያ የታገዘ የቴክኖሎጂ ግብአትና የወፍጮ ቤት አገልግሎት በመንግስት ወጪ ይሸፈናል፡፡

ለፕሮግራሙ 59 ሚሊዮን ብር በጀት የተያዘ ሲሆን ወጪው በዋናነት የሚውለው ለልማት ተቋማት ግንባታ ለወፍጮና የእርሻ መሳሪያ ግብአት ነው፡፡

የጋምቤላ ክልል ቁልፍ ችግር ድህነት ነው ያሉኝ ርዕሰ መስተዳደሩ ከክልል እስከ ወረዳና ቀበሌ ያሉት አመራር አካላትና ህዝቦች ለክልላችን የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድን ለማሳካት ተቀናጅተን በመስራት የክልላችንንና የሃገራችንን ህዳሴ ወደማይቀለበስበት ደረጃ ላይ ለማድረስ መረባረብ እንደሚኖርብን አቋም ይዘናል፤ ቃላችንንም ወደተግባር እየመነዘርን ነው ብለውኛል፡፡